# የቅንጅት አፍራሾችና ከሳሾች ወዴት ሄዱ?

አዎን ይህን ርዕስ ያነሳሁበት ምክንያት የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማና ከዚያ ወዲህ የቅንጅት መሪዎች በእስር ላይ በነበሩበት ወቅት እና ከተፈቱም በኋላ የትግሉን አቅጣጫ ነጥቀው ለመቀየር የሞከሩትን የውስጥ ጠላቶች አስመልክቶ ያደረሱት አፍራሽ ሚና እስከዛሬም ድረስ በአንዳንድ ሰዎች ህሊና ውስጥ እንዲጉላላና ለትግሉ የሚያደርጉት ተሳትፎ እና አስተዋጽኦ እንዲቀዘቅዝ ተጽእኖ ያሳደረው ነገር ስላለ ያኔ ሲደረደሩ የነበሩ የሀሰት ክሶች፣ ስም ማጥፋቶችና ግራ ማጋባቶችን ሲያካሂዱ የነበሩት ሰዎች ዛሬ ወዴት ደረሱ? ምንስ እየሰሩ ናቸው? የሚለውን በጥቂቱ ለመዳሰስና በትግል ስም  በጥፋት ጎዳና ላይ የተሰማሩትን በማጋለጥ እውነት በእውነትነቱ እንዲረጋገጥና እንዲታወቅ፤ ትክክል የሰሩትና በሀቀኝነት በመታገል ላይ ያሉትን ደግሞ ሕዝብ ለይቶ አውቆ ተገቢውን ድጋፍ ማድረጉ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

እንደሚታወቀው ሁሉ መለስ ዜናዊ በግንቦት 15 ቀን ማታ ወያኔ በሕዝብ መሸነፉን ሲረዳ በአምባገነንነት ያወጀው ያስቸኩዋይ ጊዜ አዋጅ እስከዛሬም አልተነሳም። የውስጡንም ትግል ለማዳፈን የተለያዩ ተለጣፊ ቡድኖችን መስርቶ ተቃዋሚ ክፍሉን አንቆ ሲገኝ፤ በውጭ ያለውን ትግል ደግሞ በውጭ መሳሪያዎቹ በእነ አንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ አማካኝነት የተለያዩ ካድሬዎችን በየከተማው አሰማርተው የትግሉን አቅጣጫ ለማስቀየር ሲዳክሩ ይገኛሉ። አዎን የትግሉን አቅጣጫ መቀየርና መምራት ባይችሉም ጥቂት ካድሬዎችን በገንዘብ ኃይል አሰማርተው ተለጣፊ የድጋፍ ድርጅቶችን መስርተው ግራ በማጋባት ላይ ይገኛሉ።

እነዚህ በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ የተመደቡ ካድሬዎች ብዙ ደጋፊ ያላቸው ለማስመሰል በደጋፊ አባላቱ ቁጥር ድኀረ ገጾችን፣የተለያዩ ሬዲዮና ፓልቶክ ክፍሎችን ይዘው ለማወናበድ ይሞክራሉ። ዋናው ሃይላቸው ግን የኢትዮጵያ ጠላቶች የሚሰጡዋቸው ገንዘብ ነው። በገንዘብ ጥቂት ሆዳሞችን ገዝተው ከወያኔ፣ ከሻዕቢያና ከውጭ ጠላቶቻችን ጋር የተቀነባበረ ሴራ ሲሰሩ ይታያል። ለሆዱ የተገዛው ህሊና ስለሌለው አይገርምም ሆኖም ግን አንዳንድ ሰዎች መመራመርና መጠየቅ ተስኖአቸው አብረው እንገፍ እንገፍ ማለታቸው ያሳዝናል። ከምሁሩም መካከል ለውጭ ኃይል የሚሰሩ፣ በጎጥና በዘር ልጓም የሚጎተቱ ደካሞች ዝናቸውን ወይም ሙያቸውን ከለላ አድርገው የባንዳ ስራ ሲሰሩ ይታያል።  የቅንጅቱን ፕሬዚዳንትና በውጭ ያሉትን ደጋፊዎች ሲከሱና ሲወነጅሉ የነበሩት ዛሬ ሀሰታቸው በመጋለጡ ድምጻቸውን አጥፍተዋል። ይህም ማለት አርፈው ተቀምጠዋል ማለት ሳይሆን ሌሎችን ከለላ አድርገው ተደብቀው የጥፋት ስራቸውን እንደቀጠሉ ናቸው።

እነአንዳርጋቸው ጽጌ ከብርሃኑ ነጋ ጋር ሆነው ሻዕቢያ ኢትዮጵያን ነጻ እንዲያወጣላቸው እየተመኙ የትግል መንገድ ካለ ኤርትሪያ በቀር ሌላ እንደሌለ ፕሮፓጋንዳ እየነዙ ነው። መቼም ለኢሳያስ አፈወርቂ ምንም አይሳነውም በእርሱ መጀን ብለው መላ ኢትዮጵያን ነጻ ሊያወጡልን እነ ብርሃኑ ነጋ፣ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ሙሉነህ እዩኤል፣ ዳንኤል አሰፋና ጌታሁን ቸኮል ጦር እየመሩ መጀመሪያ ጎንደርን፣ ወሎን፣ ትግራይን ከዚያ ወለጋን ጎጃምን ነጻ እያወጡ አዲስ አበባን ከበው ሲያስጨንቁ ከዚያ አዲስ አበባን "ተቆጻጸርና" የሚሉንን ቀን በናፍቆት ስንጠብቅ፡ መቼም እንደዚህ ዓይነት ቀልድ በታሪክ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅ። የማስታወቂያ ሚኒስትራቸው ሻዕቢያው ኤልያስ ክፍሌም ከዚህ ውጭ ትግል የሚያስበውን ሁሉ በሰይፍ በጎራዴ እየቀነጠሰ ሊጥለው መዘጋጀቱን በተደጋጋሚ አሰምቷል። ይህን የህጻን ልጅ ጨዋታን የመሰለ ነገር እውነት ነው ብለው የሚያምኑትንና ጊዜያቸውን የሚያጠፉትን ወደ ሀኪም ቤት ወይ ጠበል ሂዱ ከማለት በቀር ምን እንደሚባል ግራ ያጋባል። በፊትም ተናግሬያለሁ ዛሬም ሀቁን እናገራለሁ። ይህ በብርሃኑ ነጋ መሪነት የውጭውን ትግል ለማኮላሸት የተቀነባበረ የውስጥና የውጭ ሴራ ስለሆነ ከቀድሞ ታሪካቸውም ሆነ በቅርቡ ካሳዩን ተግባሮች ማንነታቸውን ህዝብ ማወቅና ተገቢውን ምላሽ ሊሰጣቸው ስለሚገባ ነው። ብርሃኑ ነጋ ትላንት ተራራ ጫፍ ላይ ነበር ዛሬ ደግሞ ኤርትሪያ በረሃ ውስጥ እየተዋጋሁ ነኝ ሊለን ይችላል። ማስተዋል የሚያስፈልገው የዚህ ቡድን መሪዎችም ሆኑ የፕሮፓጋንዳ ክፍላቸው በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ ሆኖ ነው "የሚዋጋውና የሚያዋጋው"። የኢትዮጵያ ሕዝብማ የት አውቋቸው የት ሰምቷቸው።  የኢትዮጵያ ሕዝብ የማያውቀው፣ ያልደገፈው፣ ያልተዋጋለት ትግልን መደገፍ የምትሹ መብታችሁ ነው ተሞኙ ተታለሉ ከጠላት ጋር ወግኑ። ከ6 ወር በህዋላ ደግሞ ሌላ ታሪክ ሲያወራ እንሰማ ይሆናል።

ባለፈው ዓመት በየሚዲያው የነበሩት እነ ብርሃነ መዋ፣ ሞገስ ገብረማርያም፣ ታማኝ በየነ፣ ደበበ እሸቱ (አይ ደቤማ እነ ብር  ቱካንንም ሆነ ብር  ሃኑን ጋር ሳይሆን ከስማቸው የመጀመሪያዎቹን ሁለት ፊደሎች ብቻ ይዞ  ብር ብር እንዳለ አሜሪካ መቅረቱ ነው) ኦዲተር ነኝ ባዩ አስማማው የት እንደደረሰም አይታወቅ እየተፈለገ ነው ይባላል። ምነው ያንን ተበላ ያለውን አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ማስመለስ አቃተው?

እነ ታማኝ በየነ ታማኝ የሆኑላቸውን የኪነት ሰዎች "ማኖ" እያስነኩ የታዘዙትን ይሰራሉ። ስራቸው መሳካቱን የሚያሳያው ከሰለሞን ተካልኝ ወዲህ ሌሎችንም ድምጻውያን ወይም ከያንያንን "ማኖ" ማስነካታቸው ላይ ነው።

ተለጣፊና አንጃ የተባሉት ደግሞ የድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ዋና ባለ ጉዳይ ሆነው የከሰረ መድረካቸውን ለማንሳት ደፋ ቀና ይሉበታል። በየከተማው አንጃዎችና ተለጣፊዎች ያቺን አጀንዳ ይዘው ለመሮጥ ይዋከባሉ መቼም በአገርና በድንበር ኢትዮጵያዊ ቀልድ አያውቅምና ደጋፊ እናገኛለን ብለው ነው የሚራወጡት። አገርና ዳር ድንበር መነገጃና መድረክ ማግኛ መሆኑ እጅግ ያሳዝናል።

HR 3000 ን እንደዚሁ ለመቀማትና ዋና ባለ ጉዳይ ለመሆን እነ አል፡ማርያም (ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም ) ሲራወጡ የነበረው ትዝ ይላችኋል? በውጭ አገር ያለው ፋሽን ደግሞ አንድ ሰሞን ሆይ ሆይ ይባልና ሌላ ጉዳይ ሲመጣ ደግሞ ይረሳል። እኛ ግን ብዙ ታዝበናል።አዬ የምሁር ከንቱዎች።

ወያኔ ሊወድቅ ሲንገዳገድ የሚደግፉ እነማን መሆናቸውን ማየት የጀመርነው ደግሞ ከምርጫ 97 ወዲህ ነው። በየስብሰባው ላይ እንደ ብርቅ እና ታጋይ ተደርገው ሲታዩ የነበሩት ከሃዲዎች እነ አብርሃም ያዬና አረጋዊ በርሄ ሰዬ አብርሃ ዛሬ ማንነታቸውን አሳይተውናል። የዘሬን ብተው ይዘርዝረኝ ሆነና ነገሩ ዘረኛነታቸውን ቁልጭ አድርገው አሳዩን። ከዚህ ምን እንማራለን? እውነተኛና ሀቀኛ ድኅረ ገጽ ነው ሲባል የነበረ ኢትዮ ሚዲያ ባለቤት አብርሃ በላይ ዛሬ ወዴት እንደወገነ ስናየው ጥንቃቄ እንድንወስድ ያደርገናል።

እንደ አሸን በቅርቡ የተፈለፈሉትም ድኅረ ገጾችና ፓልቶክ ክፍሎች የእነ አንዳርጋቸው ጽጌ ስራዎች መሆናቸውን ብዙዎቻችሁ ልብ አላላችሁ ይሆናል። ዋና ዓላማቸው ሚዲያውን በሰፊው ከያዝን የሕዝቡን አስተሳሰብና አቅጣጫ እናሰቀይራለን ነው። ያላሰቡት ነገር ዋናው የትግሉ መድረክ አገር ቤት መሆኑን ነው። እዚህ ደግሞ የሚንቀሳቀሱትን ግራ ለማጋባት ይችሉ እንደሆን እንጂ አብዛኛው እያያቸው ድጋፍ ሳይሰጣቸው በትዝብት እየተመለከታቸው ነው።

የእነ ብርቱካን ሚዲቅሳ አዲስ ፓርቲም ወዴትም ፈቀቅ ማለት አልቻለም፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕዝብ አልደገፈውምና ነው፡፡ ሽማግሌው ፕሮፌሰርም ሲዞሩ ከርመው ሲመለሱ ለብርቱካን እጅ ሲነሱ የሚያሳየውን ፎቶ በአገር ቤት በጋዜጣ ላይ ተመልክቼም ገረመኝ፡፡ አዲስ መሰረትን ያሉት ድርጅታቸው እንደ አሜባ ሁለት ቦታ ሊከፈል በመንገድ ላይ ነው ይባላል፡፡ ስለሆነም ብዙ የሚያሳስብ ነገር የለም፡፡ ቅንጅትም ባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ባለቤቱ እያለ ለመውረስ ማሰባቸው እነሱኑ ትዝብት ላይ ከመጣሉ በቀር የሚወርሱትም ነገር የለም፡፡ ባለቤቱ እያለ ወራሽ ነኝ ባይ ሲመጣ ዘንድሮ ብቻ ሰማን፡፡ የውጭ ደጋፊ የተባለው ከረንት አፌሩም ጠዋት ብርቱካንን ማታ ብርሃኑን ይደግፋሉ፡፡አይ ግራ መጋባት ሲያውቁበት!

ዛሬ ማን ሀቀኛ ማን ቀጣፊ እንደሆን ተመለከትን፡፡ "በቅንጅት ገንዘብ በ650 ሺህ ብር ለኢንጂነር ኃይሉ ቤት ተገዛ የተባለው ቤት ምን ሆነ? ኦዲተር ነኝ ባዩ ለተበላው ገንዘብ IRS ክስ ጀምሯል ሲለን የነበረው ጉዳይ ምን ደረሰ? ኢንጂነር ኃይሉ ቤታቸውን አከራይው አሜሪካ መቅረታቸው ነው ያሉትስ እውነት ነበር ሀሰት? እንደዚህ ባዮቹስ የት ናቸው ምንስ እየሰሩ ነው ዛሬ? አምባገነን ሲባሉ የነበሩት ኢንጂነር ኃይሉስ የቅንጅት ጠቅላላ ጉባኤ አወረዳቸው ወይስ ደግሞ መረጣቸው? ብሎ ማለት አግባብ ይመስለኛል፡፡

ሀሰቱ ወሬ በሀሰተኞቹ፣ በአፍራሾቹ፣ በአንጃዎቹ በብርሃኑ ነጋና በብርቱካን ደጋፊዎች የተወራ ከንቱ አሉባልታ ሲሆን፣ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ከህክምናቸው በኋላ አገራቸው ሲገቡ የተደረገላቸውን አቀባበል ቪዲዮ መመልከቱ የሕዝብ መሪ ምን ዓይነት አክብሮትና ፍቅር እንዳለው ያሳያል፡፡ ቅንጅት ደግሞ በወጣቱ፣ በሴቱ፣ በአዋቂው፣ በጎልማሳው ተደግፎ ጠቅላላ ጉባዔውን አካሂዶ ከመላው ኢትዮጵያ የመጡት ተወካዮች ያስተላለፉትን መልዕክት ብታዳምጡ በእርግጥም ቅንጅት የሕዝብ መሆኑን ስታረጋግጡ ኢንጂነር ኃይሉ ደግሞ ከሕዝባቸው ጋር ሆነው ትግሉን እየመሩና እየተመካከሩ ናቸው፡፡ የጉባዔውን ቪዲዮውን ከሲያትል ባልንጀራዬ ልካልኝ ተመልክቼዋለሁ፡፡ ታሪካዊና ትምህርታዊ ነው፡፡ ማየት ማመን ነው ይባል የለ፡ ተመልክታችሁ መፍረድ ትችላላችሁ፡፡

መደገፍ ያለብን በሻዕቢያ በኩል ነጻ አወጣችኋለሁ የሚለውን ሀሰተኛ የብርሃኑና አንዳርጋቸውን ቡድን ወይም በአንጃነት የሕዝብን ፓርቲ ለማፍረስ አድመው ሌላ ፓርቲ መስርተው ዛሬም የቅንጅት ወራሽ ነን የሚለው የእነ ብርቱካንን አፍራሽ ድርጅት ወይስ ቅንጅትን ከተዳከመበት አንስተው አጥርተውና አጠናክረው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚታገለውን በኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የሚመራውን ፓርቲ ? መልሱን ለእናንተ እተዋለሁ፡፡

አዳነች መኮ
ቫንኮቨር፣ ካናዳ